# CYSHCN እነማን ናቸው?

**CYSHCN የሚከተሉትን የሚያደርጉ ልጆች ናቸው፦**

- ***ሥር የሰደደ የአካል፣** የእድገት፣ የባህሪ ወይም የአእምሮ ጤና ሁኔታዎች ሊኖራቸው ወይም ሊኖርባቸው ይችላል
- በአጠቃላይ በልጆች **ከሚያስፈልገው በላይ የሆነ ዓይነት ወይም መጠን** የጤና እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ያስፈልጋቸዋል




በዋሽንግተን ግዛት ውስጥ 20% የሚሆኑት ልጆች ልዩ የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች አሏቸው



*ይህ **ከአምስት አንዱ** ነው!*

19.7% የሚሆኑት ከ 0-17 ልጆች ልዩ የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች አሏቸው

**የውሂብ ምንጭ፦** 2019-20 **ብሔራዊ የህፃናት ጤና የዳሰሳ ጥናት፣ የጤና ሀብቶች እና አገልግሎቶች አስተዳደር፣ የእናቶች እና ሕፃናት ጤና ቢሮ**

* በተፈጥሯዊ (እንደ ጄኔቲክ ሁኔታ) ወይም ሥር የሰደደ በሽታን ከመፍጠር ጋር በተያያዙ አካባቢያዊ ሁኔታዎች ምክንያት ለአደጋ የተጋለጡ ናቸው።

# አገልግሎቶችን እንዳፈላልግ ማን ሊረዳኝ ይችላል?

*አጋርነታችን ከሚከተለው ጋር ነው፦*

## *አካባቢያዊ የ CYSHCN አስተባባሪዎች*

ለቤተሰቦች የሚሟገቱ እና ከሚያስፈልጋቸው ሀብቶች እና እንክብካቤ ጋር እንዲገናኙ የሚረዱ። *እርስዎን ከሚከተሉት ጋር ለማገናኘት ሊረዱዎት ይችላሉ (እንግሊዝኛ ብቻ)* **(እንግሊዝኛ ብቻ)**፦

- የመድን ዋስትና
- በጊዜ የሆነ ጣልቃገብነት
- ላልተሟሉ ፍላጎቶች ያሉ ግብዓቶች
- ከአካል ጉዳተኝነት ጋር የተያያዙ አገልግሎቶች
- ሕክምናዎች እና ልዩ አገልግሎቶች

## *Help Me Grow Washington ነፃ የስልክ መስመር 1 (800) 322-2588*

ስለ ልጅዎ ጤና ወይም የእድገት ፍላጎቶች ጥያቄዎች አሉዎት? ከቤተሰብ ፈላጊ ጋር ለመነጋገር እና መልሶችን ለማግኘት ወደ WithinReach Help Me Grow Washington ነፃ የስልክ መስመር ይደውሉ! በአካባቢዎ ውስጥ ነፃ ወይም ዝቅተኛ ዋጋ ያላቸውን ሀብቶች እንዲያገኙ ሊረዱዎት ይችላሉ፣ ለምሳሌ፦

- የወላጅ እና የወንድም/የእህት ድጋፍ
- የጉርምስና ሽግግር ሀብቶች
- ማህበራዊ እና መዝናኛ እድሎች
- የእረፍት መረጃ
- የእድገት ምርመራዎች
- የጤና እንክብካቤ
- ...እና ሌሎችም!

በመስመር ላይ በ www.ParentHelp123.org (እንግሊዝኛ ብቻ) እርዳታን ያግኙ

## *CYSHCN የድጋፍ መልዕክት ሳጥን*

ለ CYSHCN@doh.wa.gov ኢሜይል ያድርጉ ከሰራተኞቻችን ጋር ለመገናኘት

ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለመጠየቅ፣ 1-800-525-0127 ላይ ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም የመስማት ውሱንነት ያለባቸው ደንበኞች፣ እባክዎ በ 711 (Washington Relay) ይደውሉ ወይም civil.rights@doh.wa.gov ላይ ኢሜይል ይላኩ

Washington State Department of Health
DOH 970-108 February 2022 Amharic

# *የዋሺንግተን ግዛት Children & Youth with Special Health Care Needs (CYSHCN፣ ልዩ የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች ያሏቸው ሕፃናት እና ወጣቶች)*



## *ራዕያችን*

ሁሉም CYSHCN እና ቤተሰቦቻቸው አካላዊ እና አእምሯዊ ጤንነታቸውን፣ እድገታቸውን፣ ማህበራዊ እና ስሜታዊ ደህንነታቸውን በፍትሃዊነት የሚደግፉ የተቀናጁ ተደራሽ ስርዓቶች ባሏቸው ማህበረሰቦች ውስጥ ሲሆኑ፣ ሲሳተፉ፣ እና ሲያድጉ

**doh.wa.gov/CYSHCN**

# የቤተሰብ አመራር፣ ተሳትፎ፣ እና የድጋፍ አጋሮች

**Partnerships for Action, Voices for Empowerment (PAVE) (እንግሊዝኛ ብቻ)**

በርካታ የ Partnerships for Action, Voices for Empowerment (PAVE፣ አጋርነት ለድርጊት፣ ድምፆች ለማብቃት) ፕሮግራሞች ቤተሰቦችን በሚከተለው ይረዳሉ፦

- Family to Family Health Information Center (Google ትርጉም ይጠቀማል) የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶችን ለመደገፍ ምንጮችን እንዲያገኙ ሊረዳዎት ይችላል
- Lifespan Respite WA (Google ትርጉም ይጠቀማል) ለአንክብካቤ ሰጪዎች እረፍትን (አጭር እረፍቶችን) በገንዘብ ይደግፋል
- Parent Training and Information (PTI፣ የወላጅ ስልጠና እና መረጃ) (Google ትርጉም ይጠቀማል) አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ይደግፋል
- Specialized Training of Military Parents (STOMP፣ ለወታደራዊ ወላጆች ልዩ ስልጠና) (እንግሊዝኛ ብቻ) ወታደራዊ ቤተሰቦችን ይደግፋል

**Parent to Parent (P2P፣ ወላጅ ለወላጅ) (እንግሊዝኛ ብቻ)**

በሁሉም ካውንቲ ውስጥ ያሉ የ Parent to Parent (P2P፣ ወላጅ ለወላጅ) መርሃ-ግብሮች የሚከተሉትን ያቀርባሉ፦

- አንድ ለአንድ የአቻ ድጋፍ እና ቡድኖችን ማጋራት።
- ወቅታዊ መረጃ እና ስልጠና
- አቻ ወላጅን አማክሮ የመርዳት መርሃ-ግብር
- የሲብሾፕ ፕሮግራም ለ CYSHCN ወንድማማቾች እና እህታማቾች
- መርጃ እና ሪፈራል

**Washington State Fathers Network (WSFN)**

Washington State Fathers Network (WSFN፣ የዋሺንግተን ግዛት የአባቶች አውታረ መረብ) ለአባቶች እና ለወንድ ተንከባካቢዎች እንቅስቃሴዎችን እና ዝግጅቶችን ያቀርባል

**Washington State Leadership Initiative ጋዜጣ (WSLI) (Google ትርጉም ይጠቀማል)**

የ Washington State Leadership Initiative (WSLI፣ የዋሺንግተን ግዛት የአመራር ተነሳሽነት) ጋዜጣ የ CYSHCN ቤተሰቦችን ከእንቅስቃሴዎች፣ ዝግጅቶች፣ ዌብናሮች፣ ኮንፈረንሶች፣ ስልጠናዎች፣ የበጎ ፈቃደኞች እና የስራ እድሎች እና ግብአቶች ጋር ያገናኛል።

ለ WSLI ጋዜጣ ይመዝገቡ (እንግሊዝኛ ብቻ) (እንግሊዝኛ ብቻ)





# የጤና እንክብካቤ አጋሮች



## *የ CYSHCN የአመጋገብ አውታረ መረብ*

የአመጋገብ አውታረ መረብ (እንግሊዝኛ ብቻ) ለ CYSHCN እና ለቤተሰቦቻቸው የአመጋገብ አገልግሎቶችን ይደግፋል። በልዩ ሁኔታ የሰለጠነ የስነ ምግብ ባለሙያ (RDN) ወይም ማህበረሰብ የመመገብ ቡድን (እንግሊዝኛ ብቻ) ማግኘት ይችላሉ።

## *የልዕቀት Neurodevelopmental Centers (NDCs)*

Neurodevelopmental Centers (NDCs፣ የኒዩሮዴቬሎፕመንታል ማዕከላት) (እንግሊዝኛ ብቻ) የስራ ህክምና፣ የንግግር ህክምና፣ የአካል ህክምና እና ሌሎች አጋዥ አገልግሎቶችን ይሰጣሉ። NDCs ብዙ ጊዜ ከአካባቢው አስተባባሪዎች እና ሌሎች እንክብካቤ አቅራቢዎች ጋር ይተባበራሉ።

## *Maxillofacial Review Boards*

Maxillofacial Review Boards (MFRBs፣ ማክሲሎፌሻል ምልከታ ቦርዶች) (በእንግሊዘኛ ብቻ) አቅራቢዎች የከንፈር/ላንቃ መሰንጠቅ ላለባቸው ሕፃናት እንዲያቅዱ እና የተቀናጀ ሕክምናን እንደሚያካሂዱ ያረጋግጣሉ።

## *የሕክምና ቤቶች አጋርነት መርሃ-ግብር*

ከልጅዎ ሐኪም እና ከሌሎች የልጅዎ የእንክብካቤ ቡድን አባላት ጋር እንዴት ውጤታማ አጋር መሆን እንደሚችሉ የበለጠ ለማወቅ medicalhome.org (በእንግሊዘኛ ብቻ) ን ይጎብኙ።

# ለቤተሰቦች ያሉ ሌሎች ግብዓቶች

ለቤተሰቦች ማሳወቅ (Google ትርጉም ይጠቀማል) - የእድገት እክል ያለባቸው ሰዎች ሙሉ ህይወት እንዲኖሩ ለመርዳት መረጃ እና ግብዓቶችን ያቀርባል።

Early Support for Infants & Toddlers (ESIT፣ ለጨቅላ ህጻናት እና ታዳጊዎች የቅድሚያ ድጋፍ) (እንግሊዝኛ ብቻ) - ዕድሜያቸው እስከ 3 ዓመት ለሆኑ ህጻናት የእድገት መዘግየት ወይም አካል ጉዳተኞች የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎት ይሰጣል።

Developmental Disabilities Administration (DDA፣ የእድገት አካል ጉዳቶች አስተዳደር) (እንግሊዝኛ ብቻ) - የግል እንክብካቤ እና እረፍትን ጨምሮ አገልግሎቶችን እና መርሃ-ግብሮችን ያቀርባል።

Office of Superintendent of Public Instruction (OSPI፣ የህዝብ ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ) - የት/ቤት ዲስትሪክት አገልግሎቶችን ይቆጣጠራል።

Office of the Education Ombuds (OEO፣ የትምህርት እንባ ጠባቂ ተቋም) - ከትምህርት ዲስትሪክቶች ጋር ስለ ግጭት አፈታት መረጃ ያቀርባል።

The Arc (እንግሊዘኛ ብቻ) - የአእምሮ እና የእድገት እክል ላለባቸው ሰዎች ሁሉ መብቶች ይሟገታል። አካባቢያዊ ምዕራፎች (እንግሊዝኛ ብቻ) ለቤተሰቦች መረጃን ይሰጣሉ።

Developmental Disabilities Council (DDC፣ የእድገት እክል ላለባቸው ምክር ቤት) (እንግሊዝኛ ብቻ) - የእድገት እክል ላለባቸው ሰዎች እና ለቤተሰቦቻቸው ዕቅዶችን ያወጣል።

DD Ombuds - የእድገት እክል ላለባቸው አገልግሎቶችን በሚጠቀሙ ሰዎች የሚመጡ ቅሬታዎችን ይሰበስባል እና ይመረምራል።



